# የወያኔን ጕሰኛ አገዛዝን ማሰናበት ይቻላል!

የዓለም ኃያላን መንግሥታት የራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ለወያኔ መንግሥት ታዋቂነትን በመስጠት መለስን ከለንደን የፓርቲውን ስም አስቀይረው አዲስ አበባ እ.እ.አ 1991ዓ/ም አስገቡ። ኢትዮጵያን በጕሳ አገዛዝ ሸንሽኖ ለአሥራ አራት ዓመታት ብሔራዊ አንድነታችን አናግቶ ሲገዛ፥ አገር ሲገነጥልና ሲያስገነጥል ዲሞክራሲን ከኢትዮጵያ አልፎ ለአፍሪቃ ቀንድ ያመጣ ትኩስና ወጣት መሪ ተብሎም ከፈጣሪው (ጌታው) ከኢሳይያስ አፈወርቂ ጋር በአንድ ወቅት ሲወደሱና ሲሞገሱም ነበር። አሁንም ሆነ ወደፊት ኃያላን መንግሥታት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብር መሪ ኢትዮጵያ እንዲኖራት አይፈልጉም።

ሀ/ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምን አስከባሪ መሪ የኢትዮጵያ ዳር ድንበርን የማስከበር ጥያቄ ያመጣል፥ ይህም የኤርትራንና የአሰብን ጉዳይ ይቀሰቅሳል፥ ቀጥሎም ወደ ትኩስ ጦርነት ያመራል የሚል እምነት አላቸው። ለዚህም ነው በቅርቡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን በምርጫ ሲሸኙት እነዚህ መንግሥታት ወያኔ መሸነፉን እየተረዱ እንደ መስካሪና መካሪም ከአንገት በላይ እየተናገሩ በተግባር የመለስን መንግሥት መኖር በመደገፋቸው ለወያኔ የልብ ልብ ሰጥቶታል። የሰላማዊው ሕዝብ ፍጅትንም አጋግሏል።

ለ/ ኢትዮጵያ በሕዝቧ ብዛት ከአፍሪቃ ሁለተኛ በመሆንዋ፥ አቀማመጧና የተፈጥሮ ኃብቷም ለልማት አመቺ በመሆኑ፤ እራሳችንን መቻልም ለሸቀጣቸው መጣያ ቦታ ስለሚያሳጣቸው፥ ብሎም ግሎቫላይዜሽን የተባለው ዓለምን የማስተዳደር ፕሮግራማቸው ስኬታማ ለማድረግ ጥቃቅንና ድኃ መንግሥታት ያስፈልጋቸዋል። ዛሬ በእነሱ ፕሮግራምና ፕላንም እንመራለን። ስለዚህም ለችግራችን እርዳታቸው ሥር ነቀል ለውጥ የሚያመጣ ሳይሆን ጠቃሚነቱ ጊዜያዊ ነው። ለምሳሌም ዳቦ ለዕራብተኞች ምስክራችን ነው።

በአገራችን ከብዙ መቶ ሺ በላይ ወገኖቻችን በወያኔ/ሕወሐት በእስር ቤት ናቸው። እናት፥ አባት፥ አዛውንት፥ ወጣትና ሕፃን ሳይባል ግንባራቸው ለወያኔ አጋአዚ ሠራዊት ኢላማ እየሆነ ነው። የሰው ሕይወት ክብር ያጣበት አገር ሆነች። የብዙኃን መገናኛ ጋዜጦችና መጽሔቶች ያለአግባብ ተዘግተዋል፤ ዘጋቢዎችም ታስረዋል። ከእስር የተረፉትም ተሰደዋል። የሕዝባችን ጩኼት ታፍኗል።

ቤተሰቦቻችን ላይ ፋሺስት ጣሊያን ያላደረሰባቸውን ግፍ ወያኔ እየፈጸመባቸው እንዴት ዝም ይባላል? የኢትዮጵያ ነፃነት የብሔራዊ የማንነታችንና የነፃነታችን መለያ ነው። አልፎም በአንድነት፥ ከሰብአዊ ክብርና እኩልነት አብሮ የተጠቃለለ አስተሳሰብ ላይ ሰፍሮ ግላዊ የጕሣ ጥቅምን በብሔራዊ ጥቅም ለውጦ የሕዝቦችዋን በላይነት የሚያረጋግጥ መከበሪያችን ነው።

የሕወሐት ጕጠኝነት በጕሳ ሸንሽኖን አንድነታችንን እያናጋ ነው። የኢትዮጵያን ሉኣላዊነት ለማስከበር ከጥንት ጀምሮ የተዋደቁት የመላው ኢትዮጵያ ልጆች ናቸው። አሁንም አገራችንን ከወያኔ ጕሰኛ አገዛዝ ለማዳንና የትውልድ ተልዕኮን መወጣት የሚቻለው ሁላችን እጅ ለእጅ ተያይዘን ክንዳችን በወያኔ ላይ ስናነሳ ብቻ ነው። አፍራሽ ከሆነው ጕሰኝነት፥ ቅኝ አገዛዛዊና ከፋፋይነት ሥርዓት በትግላችን መላቀቅ አለብን። ምንም እንኳ መለስ አድዋ ቢወለድም ኤርትራዊ ነው። በአገር አስገንጣይነቱ ማንነቱን አስመስክሯል። ሥርዓተ መለስን ለመገርሰስ ትግል በራሱ ዙሪያ መጀመር አለበት። ስለዚህ የትግራይ ተወላጆች ቀዳሚ ሚና መጫወት አለባቸው።

ወያኔን በሥልጣን ለማቆየት ተብሎ የኢትዮጵያን ሥነ ልቦና ማኰላሸት፥ በሕዝቦች መካካል ልዩነትን መፍጠር፥ አንድነታችንን ማፈራረስና ሕዝብን በአደባባይ በቀን ማሰረሸንና መረሸን፣ በሕዝብ የተጣላ ሥርዓትን ዕድሜ ለማራዘም የሚደረግ ትግል ነውና ያለሕዝብ ፍላጐት

ከሕዝብ ጫንቃ መፈናጠጥ አይቻልም። የማይዘልቅም የትግል ስልት መሆኑን የብዙ አገሮች ትምህርትና ተለምዶ ሰጥቶናል።

የትግራይ ሕዝብ ሆይ! ከአብራክህ የወጣሁ ነኝ ባዩ የሕወሐት/ወያኔ መሪ "የአክሱም ሐውልት ለወላይታው ምኑ ነው?"፥ "የላስታ አብያተ ክርስቲያናት ለኦሮሞው ምኑ ነው?" እንዲሁም "የጐንደር ቤተ መንግሥት ቅርሶች ለከምባታው ምኑ ናቸው?" አቶ መለስ እንዳለው ሳይሆን ኢትዮጵያዊው ወገንህ በባዶ እግሩ ከየአቅጣጫው በመምጣት በአድዋና በማይጨው ሕይወታቸውን በመሰዋት ማንነትህን ያስከበሩትን የውድ አባቶቻችን አጥንት አትርሳ። በቅርቡ ዋጋ ለአጣውም የባድሜ ጦርነት መቶ ሺ ያህል ሕይወት የተሰዋውና አጽሙ እንኳ ተለቅሞ ያልተቀበረው፥ ቤተሰቡም ያልተረዳውና ዘለላ እንባ ያልፈሰሰለት የወንድምህ አጽም ይፋረድሃል።

በምርጫ ተብዮም መለስና የአሁኑ ገዥዎች ያለ አንዳች ተወዳዳሪ አሸንፈዋል ብሎ ወደ አዲስ አበባ ለንግሥና መላካቸው ሚዛናዊነትህ አያጠያይቅ ይሆን? አጋአዚያን ወይም ምርጥ የመለሰ ልዩ የግድያ ስኳዶች የትግራይ ምልምሎች አይደሉምን? ይህ በጅምላ የትግራይ ልጆችን ለመውቀስ አይደለም። ወያኔን መቃወም የትግራይን ሕዝብ መቃወም አይደለም። ከልምድ እንዳገኘነው ወያኔን መቃወም የትግራይን ሕዝብ መቃወም አስመስለው በየቦታው የአዞ ዕንባ የሚያነቡ ብዙዎች ናቸው። የጥቂቶች የሌላ ጐሳ ኢትዮጵያውያን ሆዳምነትና አድርባይነት ተጨምሮበት የሕዝብን ትግል እያዳፈንና የወያኔን ዕድሜ እያራዘምን ያለን ከሃዲዎች ታሪክ ይፋረደናል። በኢትዮጵያዊነት ሚዛን ትግራይ ከማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል አይበልጥም፤ አያንስምም። መለሰም ከትግራይ ነፃ አውጭነት እስከ ኢትዮጵያ መሪነት የበቃው በችሎታ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን በልጦ ሳይሆን በወቅቱ የደርግን ሥርዓት ጥላቻና የዓለም የፖለቲካ ሚዛን ወደ አንድ ጐን የማዘንበሉ አጋጣሚዎች ናቸው።

ወደ ወቅቱ ችግር እንመለስና በአገራችን ምንስ መደረግ አለበት? ለሚለው በአጭሩ የሕዝብ አመጽ መዳፈን የለበትም። ሕዝብን በማሰርና በመግድል ከአገርም በማባረር ትግሉን ማስቆም አይቻልም። የሥርዓት ለውጥ ጥያቄ ስለሆነ ዛሬ ለጊዜው ቢዳፈን ነገ ይነዳል። እንዲያማ ባይሆን የዘውድ ሆነ የደርግ ሥርዓት ባልወደቀም ነበር። ስለዚህ

1ኛ/ የትግራይ ሕዝብ ትናንት የኢትዮጵያና የሕዝቧ ታሪክ ግንባታ ማዕከል እንዳልሆንክ ሁሉ ዛሬ አንድነታችንና ማኅበራዊ ህልውናችን በአንተ ስም በሚነግዱ ወያኔ/ሕወሐት መሪዎች እየፈረሰ በመሆኑ ሽማግሌ ወጣት ሳይባል ከኢትዮጵያውያን ወገኖችህ ጐን በመቆም በወያኔ/ሕወሐት ላይ ክንድህን ማንሳት ይጠበቅብሐል።

2ኛ/ የትግራይ ተወላጅ ያልሆኑ የወያኔ ሥርዓት አራማጆችና ጉርሻ ተቋዳሾች ከራሳቸው ጥቅም የኢትዮጵያን ጥቅም በማስቀደም ሕወሐት/ወያኔ እኩይ ተግባር መላቀቅና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጐን በመሰለፍ ትግሉን በወያናዊ ሥርዓት ላይ ማፋፋም ይፈለግባቸዋል።

3ኛ/ ማናችንም የኢትዮጵያ ልጆች የሰላማዊ መንገድ ወይም እንደአማራጭ በአመጽ የወያኔ/ሕወሐት ቅኝ አገዛዝ ማክተም እንዳለበት በራሳችን መተማመን አለብን። ገንዘብ ያለን በገንዘባችን፥ ዕውቀት ያለን በዕውቀታችንና በአለን ሁለንተናዊ አቅም ሁሉ ኢትዮጵያን ለማዳን በአንድነት ላይ የተመሰረተ ትግልን ማፋፋም ይጠይቃል። ነፃነት እንደመና በልመና አይመጣም። መስዋእትነትን ይጠይቃል። ኢትዮጵያን ነፃ የሚያወጧት ተቆርቋሪ ልጆቿ ብቻ ናቸው። ጆርጅ ቡሽ ወይም ቶኒ ብለየር አይደለም።

4ኛ/ ለወያኔ መጠቀሚያ መሣሪያ እዳንሆን በተቃዋሚ ኃይሎች መሃል የሚከሰቱትን ልዩነቶችን ሆኑ ቅራኔዎችን ማጥበብ።

5ኛ/ ዛሬ የዓለም የመገኛና ብዙሃን ትኩረት የሳበውን የመለስ "መንግሥት" ተብዮውን ያገጠጠና ያፈጠጠ ፋሺዚም ሥርዓት ባሕርይ ለመሸፋፈንና ሕዝቡን ከትግል ለማዘናጋት

በሕዝባችን ታሪክ ውስጥ ጥቁር ጥላ ጥሎብን የተቀበረውን የደርግ ሥርዓት ለውይይት እንደ አዲስ መድረክ ላይ ለማቅረብ የሚሞክሩ ወገኖች ለወቅቱ የትግል መድረካችን ታላቅ እንቅፋት ስለሆነ፤ ይህንን የትግል ማኮላሻ ስልታቸውን ትተን ለውቅቱ ፖለቲካ ተገቢ ነው የምንለውን የትግል አቅጣጫ ማጐልበት ይጠበቅብናል።

6ኛ/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይ ግለሰብ፥ ቡድኖች፥ የፖለቲካ ድርጅቶች፥ ሁሉ ከግል ጥቅምና ሥልጣን ጥማት ከዘረኝነትና ራስን ከማኰፈስ ተላቆ ከዘረኝነት ኢትዮጵያዊነት፥ ከግለኝነት ሕዝባዊነት በማስቀደም ለወያኔ ሰርጐ ገቦችን በር በመዝጋት ሕዝቡን በአንድ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ ማደራጀትና በመምራት አንገብጋቢ ጥያቄያችን መሆን ይገባል።

7ኛ/ ወይኔ አንድነታችንን ከሚፈታተንበት በርካታ ፈርጆች ጥቂቶቹን ብንጠቅስ በሐይማኖትና በክልሎች ድንበር (መሬት) ላይ በመሳሰሉት የሕዝባችንን አንድነት በመሰነጣጠቅና ደም በማቃባት ዋነኛው ተግባሩ ስለሆነ ሕዝባችን ይህንን የወያኔ እኩይ ተግባር ተረድቶ ከመጠፋፋት መቻቻልን ማስቀደም እንዳለበት ሕዝብን ማነቃቃት።

8ኛ/ በውጭ አገር ያሉ ሥርጭታቸው ኢትዮጵያ ሊሰሙ የሚችሉ የራድዮ ጣቢያዎችን በገንዘብ በመርዳትና ገንቢ ሃሳብ በማቅረብ ህዝብን ለትግል መቀስቀስ ተቀዳሚ ተግባራችን ይሁን።

9ኛ/ ኃያላንና የአበዳሪ አገሮችን በማሳመን በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን ፖሊሲ በማስቀየር የወያኔን የኢኰኖሚ ምንጭ ማስቀረጥ አለብን።

ተኽላይ እምቧላይ
ካሊፎርኒያ